# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)


ጥር ፲፩ ቀን ፪ ሺህ ፬ ዓ. ም
January 20, 2012

## ኢሕአፓ የኦሮሞን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት ተጠራጥሮ አያውቅም

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ታህሣስ ፳፪ ቀን ፪ ሺህ ፬ ዓ. ም (January 1, 2012) ያወጣውን የአቋም መግለጫ ተመልክቶታል። የአቋም መግለጫው በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ፤ ለእኩልነትና ለሕግ የበላይነት በሚደረገው ሀገራዊ ትግል ላይ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብሎም ያምናል። ኦነግን መሰል ድርጅቶች ከአሁን በፊት ሲከተሉት የነበረውን የመገንጠል ዓላማ ትተውና ኢትዮጵያዊነትን ተቀብለው ጭቆናንና በደልን በማስወገድ፣ በእኩልነት፣ በፍትኅዊነትና በሕግ የበላይነት ላይ የተመሠረተች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ለማድረገ በሚደረገው ትግል ከቀሩት ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ትግላቸውን እንዲያስተባብሩ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ያለመታከት ላቀረበው ጥሪ ይህ አሁን ኦነግ የደረሰበት ውሳኔና ያወጣው መግለጫ ብሩህ ተስፋ ሰጭና የተባበረ ትግልም እውን ሊሆን እንዲችል የሚረዳ መልካም ፈር ቀዳጅ ነው።

ኢትዮጵያ እንደሀገር እንድትገነባ፣ እንደሀገርም እንድትቆምና ነፃነቷንም ጠብቃ እንድትኖር በትውልዳቸው ከተለያዩ ብሄረሰቦቿ የመነጩ ልጇቿ አሰፈላጊውን ሁሉ መስዋዕትነት ከፍለዋል፤ በዚህም ሂደት የኦሮሞ ሕዝብ ጉልህ አስተዋፅዖ አበርክቷል። ሀገራችን ለውጥን አርግዛ አብዮታዊ እንቅስቅሴ በፈነዳበት ወቅትም፣ የሁሉንም ዜጎቿን መብት ለማስከበር ልጆቿ በሚናገሩት ቋንቋና በመጡበት አካባቢ ሳይከፋፈሉ፣ በትከሻቸው ላይ የተጫነውን የግፍ ቀንበር ለማስወገድ በአንድነት ታግለዋል። በየራሳቸው የአካባቢ ችግሮች ብቻ ሳይወሰኑ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ ነዋሪ በሆነው ሕዝብ ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው ጭቆና፤ የጋራ ጭቆና እንደሆነ በማመን በጋራ ተነስተው፣ በጋራ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። የሕዝባችን ሕይወት እንዲለወጥና እንዲሻሻል፣ ከማንኛውም ዓይነት ጭቆና እንዲላቀቅ፣ መብቶቹንም እንዲቀዳጅ ብለው የተነሱት፣ የታገሉትና የተሰውት ወጣት ኢትዮጵያውያን በቁጥራቸው አዕላፍ ነበሩ። የ1966 ዓ. ም አብዮት ካነሳቸውና ከመሬት ጥያቄ ጋር በተዛማጅ መፈታትም የነበረባቸውን የዴሞክራሲን፣ የዕድገትን፣ የእኩልነትን፤ የፍትኅንና መሰል ጥያቄዎችን እንደጀመርነው አብረን ታግለን ልንፈታቸው በተገባን ነበር፣ የሚያዳግተን ሊሆን ባልቻለም ነበር። አሁንም ከተባበርን በዜጎቿ እኩልነት ላይ የተመሠረተችና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ዴሞክራሲያዊት አንድ ኢትዮጵያን እውን ማድረግ አያዳግተንም፤ ይቻላልም እንላለን።


**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Siver Spring , MD 20910**

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 301-578-4466** **Fax: 301-449-8363** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ሀገራችንን በሥልጣን ከባለጉት የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች መዳፍ ለማላቀቅ፣ የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ፣ አንድነቷና ክብሯን ጠብቀን ለማቆየት፣ ሀገራዊ ሉዓላዊነቷን ለማስመለስ፣ ዳር ድንበሯን ለማስከበር፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በማስፈንም የሕዝቡን ዘላቂ ጥቅሞች ለማረጋገጥ እንዲቻል ዛሬም ኢትዮጵያዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ በአንድነት ከመታገል ውጭ ሌላ መፍትሄ የለም እንላለን። ይህን አማራጭ የሌለውን ግዙፍ ሀገራዊ ዓላማ ለማሳካት የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ነውና አሁንም እንደቀድሞው በጋራ እንዲታገል በመሥራት ሁላችንም የዜግነት ግዴታችንን ለመወጣት እንነሳ! በተናጠል የሚደረግ ትግል አድካሚ፤ እልህ አስጨራሽና ውጤቱም አስተማማኝ ባለመሆኑ፣ ከኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመታገል የወሰነው ኦነግ ዛሬ የትግል አጋራችን ሊሆን በመቻሉ እሰየው እንላለን።

በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ የወሰደውን አቋም የማትጋሩ የኦነግ አባላትም ቆም ብላችሁ አቋማችሁን እንደገና በመመርመር ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መሠለፍ የሚያኮራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉልህ አካል የሆነውን የኦሮሞን ሕዝብ ሙሉ መብት ለማጎናጸፍና ጥቅሙንም ለማስከበር የተሻለው መንገድ መሆኑን ተቀብላችሁ የአንድነቱን ጎራ በማጠናከር በጋራ ታግለን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት እንድንችል ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ለአንድ ዓመት ከአሥር ወራት ከፖለቲካና ከሲቪክ ድርጅቶች እንዲሁም ከታዋቂ ሀገር ወዳድ ግለሰቦች ጋር ለአንድ ሁሉንም ለሚያቅፍ፤ ዴሞክራሲያዊና ለሀገር አንድነት የቆመ ኅብረት ምሥረታ በመሥራት ላይ ይገኛል። ሁሉንም ድርጅቶች ያለመታከት መቅረብና ማነጋገር አስፈላጊ ነው ብሎም ያምናል። ስለዚህም በተቃዋሚነት ተሠልፈን የህወሓት/ኢሕአዴግን መንግሥትና ሥርዓት ተቃውመን በመታገል ላይ ያለነው ኃይሎች ሁሉ ልንሰባሰብ፣ በጋራ መክረንና በአንድ ኅብረት ውስጥም ተደራጅተን የሕዝባችንን ብሶት በጋራ ልንቀርፍ ይገባናል እንላለን።

**በአንድነት ኃይሎች የተባበረ ትግል ዴሞክራሲ፣ ፍትኅ፤ እኩልነትና የሕግ የበላይነት በኢትዮጵያችን ውስጥ ይረጋገጣል!**